# መሃሉ ዳር ሆነ

የማነው ይህ ባንዳ ፤ የተውሸለሸለ
አገር የሚሸጠው ፤ እያፈናቀለ
ባገር በደብሩ ፤ ይመስለው የሌለ
የት ቦታ ተዘርቶ ፤ የት ነው የበቀለ
አገርም እንደሰው ፤ ቂጥኝ አበቀለ ::

ሰሜኑን ሻቢያ ፤ ምዕራቡን ድርቡሹ
መሀሉን ቻይናዎች ፤ ገብተው ሲያበላሹ
ጥጋብ አልችል ብለው ፤ በህዝብ ሲያቀረሹ
አገር አልዳነችም ፤ ቢሮጡ ቢሸሹ
ምን መተት ቢይዙ ፤ ወንዱን አኮላሹ?

ህንዱ ፣ አረቡ ፤ ቻይናው ፣ እየተጀነነ
ሰው አገሩን ለቆ ፤ ስደት ተበተነ
ዳር ዳሩን ቆራርሶ ፤ እየሸነሸነ
የጠላት ቡና ቁርስ ፤ ሆኖ ተዘገነ
ዳሩም አለቀና ፤ መሃሉ ዳር ሆነ ።

ገበሬው ከርስቱ ፤ ተነቅሎ ተገፍቶ
ባረብና በህንድ ፤ እህሉ ተመርቶ
ተጭኖ ይሄዳል ፤ በመርከብ ተሞልቶ
ለአመጽ መነሳት ፤ አቅቶት ተኝቶ
ሌላውን ያበላል ፤ እሱ በራብ ሞቶ ።

ሰው በገዛ አገሩ ፤ ተይዞ በጠኔ
አረብ ይቀልባል ፣ አጅሬ ወያኔ
ሞት ሁለቴ የለ ፤ ምን ነካው ወገኔ
በምን ጫንቃ ቻለው ፤ ይህንን ጭካኔ
ተኝቶ ተገዛ ፤ ለዚህ አረመኔ ።

አገሬ ኢትዮጵያ ፤ ሕንድ አይደለች ቻይና
ጅዳም አትሆንም ፤ የአረብ መዲና
የባንዳ ልጅ ባንዳ ፤ ባለቀን ሆነና
አምርታ እየሰጠች ፤ ትብላ ወይ ለምና ።

ታዛቢው

August 26/2009